# ድርሐ አርያም

ጻድቅሰ ከመ በቀልት ይፈሪ። መዝ. ፺፩፥፲፪ ጻድቅ እንደ ዘንባባ ያፈራል። መዝ. 91፡12

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ርእሰ አድባራት ጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል
2601 Minnehaha Ave, Minneapolis, MN 55406 Tel: 612-913-7000

ሰኔ ፳፻፱ ዓ.ም/ቅጽ፩/ቁጥር ፲፩ ወርኃዊ ጋዜጣ June 2017/Volume 1/Issue 11


## መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ



### በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ቤተሰብ

- ሕፃኑም ዮሐንስ በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና፥ የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም፤ ገናም በእናቱ ማኅፀን ሳለ **መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል**። (ሉቃ ፩፥፲፭)
- ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፅንሱ በማኅፀንዋ ውስጥ ዘለለ፤ በኤልሳቤጥም **መንፈስ ቅዱስ ሞላባት**። (ሉቃ ፩፥፵፩)
- አባቱ ዘካርያስም **መንፈስ ቅዱስ ሞላበትና** ትንቢት ተናገረ። (ሉቃ ፩፥፷፯)

መጽሐፍ ቅዱስ የዚህን ታላቅ ቤተሰብ ታሪክ በሉቃስ ወንጌል ላይ ካህኑ ዘካርያስ እና ከካህኑ ከአሮን ወገን የሆነች ኤልሳቤጥ ሁለቱም በጌታ ትእዛዝና ሕግጋት ሁሉ ያለ ነቀፋ እየሄዱ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ በማለት ይገልፃል። የመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ የልደት ታሪክም እንዲህ በሚለው በቅዱስ ገብርኤል ብሥራት ይጀምራል፦ ***ዘካርያስ ሆይ፥ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ ሚስትህ ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፥ ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ። ደስታና ተድላም ይሆንልሃል፥ በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል። በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና፥ የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም፤ ገናም በእናቱ ማኅፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል፤ ከእስራኤልም ልጆች ብዙዎችን ወደ ጌታ ወደ አምላካቸው ይመልሳል። እርሱም የተዘጋጁትን ሕዝብ ለጌታ እንዲያሰናዳ፥ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልስ ዘንድ በኤልያስ መንፈስና ኃይል በፊቱ ይሄዳል። (ሉቃ ፩፥፲፫-፲፯)***

የእግዚአብሔርን ትእዛዝና ሕግጋት እየጠበቀ በቅድስና ይኖር የነበረው ካህኑ ዘካርያስ ከእግዚአብሔር ተልኮ የመጣውን የቅዱስ ገብርኤል ቃል ባለመስማቱ ሕፃኑ እስከሚወለድ ድረስ ድዳ እንደሚሆን በአብሳሪው መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ተነገረው። ይወለዳል የተባለው መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስን የኤልሳቤጥ መፅነስ በቤተሰቡ መካከል ለረጅም ጊዜ ይፈለግ የነበረ ስለነበር ደስታ ሲፈጥር የካህኑ ዘካርያስ ድዳ መሆን ደግሞ ቤተሰቡን የሚያስጨንቅ ሌላ ክስተት ሆነ። ቅድስት ኤልሳቤጥም ባለመውለዷ ምክንያት በአካባቢው ሰዎች ግን እግዚአብሔር እንዳዘነባትና ልጅ እንደከለከላት ይነገርባት ስለነበር የልምላሜዋ ዘመን ካለፈ በኋላ መፅነስ በመቻሏ **ነቀፌታዬን ከሰው መካከል ያስወግድልኝ ዘንድ ጌታ በተመለከተበት ወራት እንዲህ አድርጎልኛል** (ሉቃ ፩፥፳፭) በማለት ደስታዋን ገልፃለች።

አስቀድሞ በነቢዩ በኢሳይያስ የአዋጅ ነጋሪ ቃል ተብሎ እንደተነገረው ***የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ ጥረጉ፥ ለአምላካችንም ጎዳና በበረሀ አስተካክሉ*** በማለት ፊት አውራሪ ሆኖ የሚላከውን ቅዱስ ዮሐንስን የፀነሰችው ቅድስት ኤልሳቤጥ በፀነሰች በስድስተኛው ወር እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ልትጠይቃት ወደ እርሷ በሔደች ጊዜ እጅግ የሚያስገርም ሁኔታ ተፈጠረ። ይኸውም ቅዱስ ዮሐንስ በማኅፀን ውስጥ ኾኖ ለቅድስት ድንግል ማርያም እና በማኅፀኗ ላለው ለዓለም መድኃኒት ለኢየሱስ ክርስቶስ ሰግዷል (ሉቃ. ፩፥፴፯-፵፩) ። . . . ወደ ገጽ 4 ይቀጥላል

*በቤተ ክርስቲያናችን ድረ ገጽ ላይ ጋዜጣችንን ለማንበብ፦ www.minnesotaselassie.org/newsletter/*

### ማውጫ


| ዝርዝር | ገጽ |
|---|---|
| 1) መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ | 1 |
| 2) ብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ | 2-3 |
| 3) ቁርባን ከተቀበሉ በፊትና በኋላ የሚጸለይ ጸሎት | 4 |
| 4) መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥያቄ | 5 |
| 5) የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እና ጤና | 6 |
| 5) ዜና ርእሰ አድባራት | 7 |
| 6) የሰበካ ጉባኤ መልእክት | 8 |
| 7) ማስታወቂያ | 8 |



**እዘጋጆች**

ሊቀ ብርሃናት ቀሲስ ሄኖክ ያሬድ
ዶ/ር ሰሎሞን ፍሌ
ወ/ሮ ሰብለወንጌል ደምሴ
ወ/ት ዘመናይ በጋሻው
አቶ አብርሃም ሰሎሞን
ዶ/ር ኤልያስ አያና

**አርታእያን**

መልአከ አርያም ቆሞስ አባ
ኃይለሚካኤል ሙላት
ሊቀ ብርሃናት ቀሲስ ሄኖክ ያሬድ

**ዲዛይን**

አቶ ውብሸት አየለ
ዶ/ር ሰሎሞን ፍሌ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በየዓመቱ ሐምሌ ፭ ቀን ጴጥሮስ ወጳውሎስ በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መልካሙን የክርስትና ገድል ተጋድለው ሰማዕትነት የተቀበሉበትን ቀን በታላቅና በተለየ ሁኔታ ታከብራለች። ክርስትናን በማስፋፋት ከፍተኛውን ሚና የተጫወቱት እነዚህ ቅዱሳን አባቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መልእክታትን ጽፈዋል። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ስምንት ምዕራፎችን የያዘ ሁለት መልእክታትን ሲጽፍ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ አንድ መቶ ምዕራፎችን የያዘ አሥራ-አራት መልእክታትን ጽፏል። ለአግልግሎት የጠራቸውም የክብር ባለቤት የሆነው አምላካችን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።



ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ዓሣ በማጥመድ ሥራ ላይ ሳለ ለዚህ ታላቅ አገልግሎት ሲጠራ (ማቴ ፬፥-፲፰) ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ ቤተክርስቲያን እና የክርስቶስ ተከታዮችን በማሳደድ ላይ ሳለ ሳውል ሳውል፥ ስለ ምን ታሳድደኛለህ? አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ፤ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብስብሃል (ሐዋ. ፱፥፬-፭) በሚል አጠራር የተጠራ ነው።

እነዚህ ሁለት ቅዱሳን አባቶች ብዙ የሚመሳሰሉበት ነገር ቢኖራቸውም ብዙ የማይመሳሰሉባቸው ነገሮችም አሏቸው። ነገር ግን ሁለቱም በአምላካችን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ተጠርተው ሰማያዊ አገልግሎትን በምድር ሆነው አሳይተውናል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ቀድሞ ለአገልግሎት የተጠራው ጌታችን በምድር ላይ ሳለ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ ከጌታ ዕርገት በኋላ የተጠራ ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ያገባ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ ያላገባ ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ መጽሐፍ የማያውቅና ያልተማረ ነው። መጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ይለናል፦ ***(የካህናት አለቆችና ሹማምንቶች ጴጥሮስና ዮሐንስም በግልጥ እንደ ተናገሩ ባዩ ጊዜ፥ መጽሐፍን የማያውቁና ያልተማሩ ሰዎች እንደ ሆኑ አስተውለው አደነቁ።) ሐዋ. ፬፥፲፫*** ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ ፈጽሞ የተማረና ሕግንም ጠንቅቆ ያውቅ የነበረ ሰው ነው። መጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ይለናል፦ ***(እኔ የኪልቅያ በምትሆን በጠርሴስ የተወለድሁ፥ በዚችም ከተማ በገማልያል እግር አጠገብ ያደግሁ፥ የአባቶችንም ሕግ ጠንቅቄ የተማርሁ፥ ዛሬውንም እናንተ ሁሉ እንድትሆኑ ለእግዚአብሔር ቀናተኛ የሆንሁ አይሁዳዊ ሰው ነኝ።) ሐዋ. ፳፪፥፫***

እንግዲህ በእግዚአብሔር ፊት እግዚአብሔርንና ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ቀድሞ መጠራት፣ በጋብቻ መኖርና፣ መጽሐፍን ጠንቅቆ አለማወቅ መመዘኛ ሊሆን አይችልም። በአንፃሩም በመጨረሻው ሰዓት መጠራት፣ በጋብቻ አለመያዝ እና መጻሕፍትን ጠንቅቆ ማወቅ መመዘኛ ሊሆን አይችልም። በፈቃደ እግዚአብሔር መኖርና የእግዚአብሔርን ሕግ በሚገባው ተከትሎ መገኘት ካለ ያገባም ያላገባም፣ የተማረም ያልተማረም እንዲሁም ቀድሞ የተጠራም አመሻሽቶ የተጠራም ሁሉም በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አላቸው።

ሁለቱ ሐዋርያት ከአጠራራቸው ጀምሮ የተለያየ ሁኔታ ቢታይባቸውም ለእግዚአብሔር አገልግሎት ግን በተሰጣቸው የሥራ ድርሻ በታማኝነት ያገለገሉ ናቸው። ከላይ በመግቢያው ላይ እንደገለጽነው ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የሚመሳሰሉበት ሁኔታ ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል፦

## ፩- ሁለቱም አይሁዳውያን ናቸው፦

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ አይሁዳዊ ለመሆኑ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የጻፈውን መልእክት ስንመለከት እንዲህ ይለናል፦ ነገር ግን እንደ ወንጌል እውነት በቅንነት እንዳልሄዱ ባየሁ ጊዜ በሁሉ ፊት ኬፋን፦ አንተ አይሁዳዊ ሳለህ በአይሁድ ኑሮ ያይደለ በአሕዛብ ኑሮ ብትኖር፥ አሕዛብ በአይሁድ ኑሮ ሊኖሩ እንዴት ግድ አልሃቸው? አልሁት። (ገላ. ፪፥፲፬)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አይሁዳዊ ለመሆኑ እንዲህ በማለት ባስተላለፈው መልእክት ለማወቅ ይቻላል፦ በስምንተኛው ቀን የተገረዝሁ፥ ከእስራኤል ትውልድ፥ ከብንያም ወገን፥ ከዕብራውያን ዕብራዊ ነኝ፤ ስለ ሕግ ብትጠይቁ፥ ፈሪሳዊ ነበርሁ፤ (ፊልጵ.፫፥፭)

## ፪- ሁለቱም በጌታ የተጠሩ ናቸው፡-

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ የተጠራው አሳ ሲያጠምድ ነው። ጌታ በገሊላ ባሕር አጠገብ ሲመላለስም ሁለት ወንድማማች ጴጥሮስ የሚሉትን ስምዖንን ወንድሙንም እንድርያስን መረባቸውን ወደ ባሕር ሲጥሉ አየ፥ ዓሣ አጥማጆች ነበሩና። እርሱም። በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ አላቸው። እነርሱም ወዲያውኑ መረባቸውን ትተው ተከተሉት። (ማቴ. ፬፡ ፲፰-፳)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በጌታ የተጠራው ወደ ደማስቆ ይጓዝ በነበረበት ጊዜ ነው። ሳውል ግን የጌታን ደቀ መዛሙርት እንዲገድላቸው ገና እየዛተ ወደ ሊቀ ካህናት ሄደ፥ በዚህ መንገድ ያሉትንም ሰዎች ወንዶችንም ሴቶችንም ቢያገኝ፥ እያሰረ ወደ ኢየሩሳሌም ያመጣቸው ዘንድ በደማስቆ ላሉት ምኵራቦች ደብዳቤ ከእርሱ ለመነ። ሲሄድም ወደ ደማስቆ በቀረበ ጊዜ ድንገት በእርሱ ዙሪያ ከሰማይ ብርሃን አንጸባረቀ፤ በምድርም ላይ ወድቆ ሳለ። ሳውል ሳውል፥ ስለ ምን ታሳድደኛለህ? የሚለውን ድምፅ ሰማ። ጌታ ሆይ፥ ማን ነህ? አለው። እርሱም። አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ፤ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብስብሃል አለው። (ሐዋ. ፱፡፩-፭)

## ፫- ሁለቱንም ጌታ ስማቸውን ለውጦታል፡-

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ አስቀድሞ የዮና ልጅ ስምዖን ተብሎ ይጠራ ነበር። (ዮሐ. ፳፩፡፲፭) ጌታም ጴጥሮስ ብሎ ስያሜ አወጣለት። <u>የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥</u> በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ። እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም። (ማቴ. ፲፮፡፲፯-፲፰) ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አስቀድሞ ለአገልግሎት ሲጠራ ስሙ <u>ሳውል</u> ተብሎ ይጠራ ነበር። በምድርም ላይ ወድቆ ሳለ ሳውል ሳውል፥ ስለ ምን ታሳድደኛለህ? የሚለውን ድምፅ ሰማ። (ሐዋ. ፱፡፬) በአገልግሎቱ ጽናት ጳውሎስ የሚል ስያሜ ተሰጠው።

## ፬- ሁለቱም ድንቅና ተአምራትን አድርገዋል፡-

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ስላደረገው ድንቅ እንዲህ ተብሎ በቅዱስ መጽሐፍ ተጽፏል፡- ጴጥሮስም በየስፍራው ሁሉ ሲዞር በልዳ ወደሚኖሩ ቅዱሳን ደግሞ ወረደ። በዚያም ከስምንት ዓመት ጀምሮ በአልጋ ላይ ተኝቶ የነበረውን ኤንያ የሚሉትን አንድ ሰው አገኘ፤ እርሱም ሽባ ነበረ። ጴጥሮስም። ኤንያ ሆይ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሃል፤ ተነሣ ለራስህም አንጥፍ አለው። ወዲያውም ተነሣ። በልዳና በሰሮናም የሚኖሩ ሁሉ አይተውት ወደ ጌታ ዘወር አሉ። (ሐዋ.፱፡፴፪-፴፭)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ታላላቅ ተአምራቶችና ድንቅ ስለማድረጉ፡- እግዚአብሔርም በጳውሎስ እጅ የሚያስገርም ተአምራት ያደርግ ነበር፤ ስለዚህም ከአካሉ ጨርቅ ወይም ልብስ ወደ ድውዮች ይወስዱ ነበር፥ ደዌያቸውም ይለቃቸው ነበር ክፉዎች መናፍስትም ይወጡ ነበር። (ሐዋ. ፲፱፡፲፩-፲፪)

## ፭- ሁለቱም ሙታንን አሥነስተዋል፡-

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ጣቢታ የተባለችውን ብላቴና ስለማሥነሳቱ፡- በኢዮጴም ጣቢታ የሚሉአት አንዲት ደቀ መዝሙር ነበረች፥ ትርጓሜውም ዶርቃ ማለት ነው፤ እርስዋም መልካም ነገር የምላባት ምጽዋትም የምታደርግ ነበረች። በዚያም ወራት ታመመችና ሞተች፤ ጴጥሮስም ሁሉን ወደ ውጭ አስወጥቶ ተንበርክኮም ጸለየ፥ ወደ ሬሳውም ዘወር ብሎ። ***ጣቢታ ሆይ፥ ተነሺ አላት። እርስዋም ዓይኖችዋን ከፈተች ጴጥሮስንም ባየች ጊዜ ተቀመጠች። እጁንም ለእርስዋ ሰጥቶ አስነሣት፤ ቅዱሳንንና መበለቶችንም ጠራ ሕያውም ሆና በፊታቸው አቆማት። (ሐዋ. ፱፡፴፮-፵፩)***

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አውጤኪስን ከሞት ስለማሥነሳቱ፡- አውጤኪስ የሚሉትም አንድ ጎበዝ በመስኮት ተቀምጦ ታላቅ እንቅልፍ አንቀላፍቶ ነበር፤ ጳውሎስም ነገርን ባስረዘመ ጊዜ እንቅልፍ ከብዶት ከሦስተኛው ደርብ ወደ ታች ወደቀ፥ ሞቶም አነሡት። ***ጳውሎስም ወርዶ በላዩ ወደቀ፥ አቅፎም። ነፍሱ አለችበትና አትንጫጩ አላቸው። ወጥቶም እንጀራ ቆርሶም በላ፤ ብዙ ጊዜም እስኪነጋ ድረስ ተነጋገረ እንዲህም ሄደ። ብላቴናውንም ደኅና ሆኖ ወሰዱት እጅግም ተጽናኑ። (ሐዋ. ፳፡፯-፲፪)***

## ፮- ሁለቱም የሰማዕትነት አክሊል አግኝተዋል፡-

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በስልሣ ሰባት ዓ.ም. በኔሮን ቄሣር እጅ ቁልቁል ተሰቅሎ ሕይወቱን አጥቷል (ሰማዕትነትን ተቀብሏል)። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በስልሣ ሰባት ዓ.ም. በኔሮን ቄሣር እጅ አንገቱን ተቆርጦ ሕይወቱን አጥቷል (ሰማዕትነትን ተቀብሏል)

የቅዱሳኑ በረከት ዘወትር ከእኛ ጋር ይሁን

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!!

አብርሃም ሰሎሞን

ምንጭ፡-

መጽሐፍ ቅዱስ
ጥሩ ምንጭ (ኀሩይ ወልደ ሥላሴ) ፲፱፻፺፫
SAINT PETER AND PAUL
(POPE SHENOUDA)

ሕፃኑም ከተወለደ በኋላ አባቱ ካህኑ ዘካርያስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ እንደዚህ አለ፡- ደግሞም አንተ ሕፃን ሆይ፥ የልዑል ነቢይ ትባላለህ፥ መንገዱን ልትጠርግ በጌታ ፊት ትሄዳለህና፤ እንደዚህም የኃጢአታቸው ስርየት የሆነውን የመዳን እውቀት ለሕዝቡ ትሰጣለህ፤ ይህም ከላይ የመጣ ብርሃን በጐበኘበት በአምላካችን ምሕረትና ርኅራኄ ምክንያት ነው፤ ብርሃኑም በጨለማና በሞት ጥላ ተቀምጠው ላሉት ያበራል እግሮቻችንንም በሰላም መንገድ ያቀናል። (ሉቃ ፩፥፷፯-፸፱)

በዚያም ዘመን ሄሮድስ የአምላካችን፣ የጌታችንና የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መወለድ ከሰብአ ሰገል ሲሰማ መንግሥቴን ይወስድብኛል ብሎ በመፍራቱ የቤተልሔም ሕፃናትን መግደል የመጀመርያ ውሳኔው ሆነ። (ማቴ. ፪፥፩-፲፮) ቅድስት ኤልሳቤጥም ልጇን ዮሐንስን ይዛ ወደ ምድረ በዳ ተሰደደች። የአዋጅ ነጋሪው ቃል ተብሎ የተነገረለት ቅዱስ ዮሐንስ ጊዜው ሲደርስ ከነበረበት በረሐ ድምፁን እያሰማ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ! እያለ እየሰበከ በዮርዳኖስ ዙሪያ ወዳለው አገር ሁሉ ወጣ። (ሉቃ. ፫፥፫-፮) ።

በስብከቱም እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ፤ መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ኹሉ ይቈረጣል፤ ወደ እሳትም ይጣላል፤ ሁለት ልብስ ያለው ለሌለው ያካፍል፤ ምግብም ያለው እንዲሁ ያድርግ፤ ከታዘዘላችሁ አብልጣችሁ አትውሰዱ፤ በማንም ላይ ግፍ አትሥሩ፤ ማንንም በሐሰት አትክሰሱ፤ ደመወዛችሁም ይብቃችሁ፤ ይል ነበር። (ሉቃ. ፫፥፯-፲፬) ።

የትሕትና አባት የሆነው ቅዱስ ዮሐንስ ጌታ ሊጠመቅ ወደ እርሱ ሲመጣ እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል፤ አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? በማለት የጌታችንን አምላክነት ፍጹም በሆነ ትሕትና ተናግሯል (ማቴ. ፫፥፲፬) ። ብዙ ተከታይ የነበረውና በስብከቱ የብዙ ሰዎችን ቀልብ የገዛው ቅዱስ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው፤ ቆሞ የሚሰማው ሚዜው ግን በሙሽራው ድምጽ እጅግ ደስ ይለዋል። እንግዲህ ይህ ደስታዬ ተፈጸመ። እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል። (ዮሐ ፫፥፳-፱-፴) በማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር የሚገባውና ከሁሉ የበለጠ ሙሽራ መሆኑን ተናግሯል። መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ካህን፣ መምህር፣ ሐዋርያ፣ ባሕታዊ፣ ነቢይ፣ ጻድቅ እና ሰማዕት ነው። ሊቁም ከሰማይ መላእክት ወገንም ሆነ በምድር ካሉ ቅዱሳን፣ ነቢያት፣ ካህናት፣ መምህራንና ሐዋርያት መካከል ማንም እንደ ቅዱስ ዮሐንስ መለኮትን ለማጥመቅ የተመረጠ አለመኖሩን በመጥቀስ **ዮሐንስ ሆይ ራጉኤል በትጋቱ፣ ኢዮብም በጽድቁ ቢመኙም ሆነ ቢጨነቁ እንደ አንተ የሚነድ እሳትን (መለኮትን) ሊያጠምቁ አልተቻላቸውም** ሲል ተናግሮለታል። (መልክአ ዮሐንስ መጥምቅ) ።

ሰኔ ፴ ቅዱስ ዮሐንስ የተወለደበትን ቀን ቤተ ክርስቲያን በቅዳሴ እና ታቦት በማውጣት ታከብራለች። በጌታ የተወደደ እና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሆኖ አምላክን ለማጥመቅ የታደለው የቅዱስ ዮሐንስ ረድኤት አይለየን፣ መንፈስ ቅዱስን ተሞልተው ድንቅ ያደረጉና ሕያው ምስክርነትን የሰጡት የመላው ቤተሰብ በረከትም ከሁላችን ጋር ይሁን።

ምንጭ፡- መጽሐፈ ስንክሳር፤
ገድለ ዮሐንስ መጥምቅ።
ሊቀ ብርሃናት ቀሲስ ሄኖክ ያሬድ

# ቅዱስ ቁርባን ከመቀበል አስቀድሞ እና ቅዱስ ቁርባን ከተቀበሉ በኋላ የሚጸለይ ጸሎት

**ቅዱስ ቁርባን ከመቀበል አስቀድሞ ከቅዱስ ምሥጢር የሚቀበሉ ሁሉ እንዲህ ይበሉ፤**

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! ርኵስት ከሆነች ከቤቴ ጠፈር በታች ትገባ ዘንድ የሚገባኝ አይደለም።
እኔ አሳዝኜሃለሁና በፊትህም ክፉ ሥራ ሠርቻለሁና በአርኣያህና በአምሳልህ የፈጠርኸው ሥጋዬንና ነፍሴን ትእዛዝህን በማፍረስ አሳድፌአለሁና ሥራም ምንም ምን የለኝምና።

ነገር ግን ስለ መፍጠርህና እኔን ለማዳን ሰው ስለ መሆንህ፣ ስለ ክቡር መስቀልህም፣ ማሕየዊት ስለ ምትሆን ስለ ሞትህ፣ በሦስተኛው ቀን ስለ መነሣትህም ጌታዬ ሆይ ከበደልና ከመርገም ሁሉ፣ ከኃጢአትና ከርኵሰትም ሁሉ ታነጻኝ ዘንድ እለምንሃለሁ እማልድሃለሁም።

የቅድስናህንም ምሥጢር በተቀበልኩ ጊዜ ለወቀሳ ለመፈራረጃ አይሁንብኝ ማረኝ ይቅርም በለኝ እንጂ።
የዓለም ሕይወት ሆይ! በእርሱ የኃጢአቴን ሥርየት የነፍሴንም ሕይወት ስጠኝ እንጂ። በሁለት ወገን ድንግል በምትሆን በወለደችህ በእመቤታችን በቅድስት ማርያም፣ በመጥምቁ በዮሐንስም አማላጅነት፣ ክቡራን በሚሆኑ በመላእክትም፣ በሰማዕታትና፣ ለበጎ ነገር በሚጋደሉ በጻድቃንም ሁሉ ጸሎት እስከ ዘላለሙ ድረስ አሜን።

**ቅዱስ ቁርባን ከተቀበሉ በኋላ በአፍ ሳለ ሁሉም እያንዳንዱ እንዲህ ይበል፤**

"ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሥሉስ ዘኢይትነገር ሀበኒ ከመ እንሣእ ለሕይወት ዘንተ ሥጋ ወደመ ዘእንበለ ኩነኔ ሀበኒ እግበር ፍሬ ዘያሠምረከ ከመ አስተርኢ በስብሐቲከ ወእሕየው ለከ እንዘ እገብር ዘዚአከ ፈቃደ በተአምኖ እጼውዐከ አበ ወእጼውዕ መንግሥተከ ይትቀደስ እግዚኦ ስምከ በላዕሌነ፣ እስመ ኃያል አንተ እኩት ወስቡሕ ወለከ ስብሃት ለዓለመ ዓለም"

ትርጉሙ፡- የማይነገር ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሦስት የምትሆን ይህን ሥጋና ደም ሕይወት ሊሆነኝ ሳይፈረድብኝ እቀበል ዘንድ ስጠኝ። በጌትነትህ እንድገለጽ ደስ የሚያሰኝህን ፍሬ እሰራ ዘንድ ስጠኝ የአንተንም ፈቃድ እየሰራሁ እኖርልህ ዘንድ ስጠኝ። በማመን አባት ብዬ እጠራሃለሁ መንግሥትህንም እጠራለሁ። አቤቱ ስምህ በእኛ ላይ ይመስገን ምስጉን ክቡር የምትሆን ኃያል አንተ ነህና ለአንተ ክብር ይገባሃል ለዘላለሙ!

ምንጭ፡- መጽሐፈ ቅዳሴ

፩- በገሊላ ባሕር አጠገብ አሳ በማጥመድ ላይ ሳለ የተጠራው፡-

ሀ) ቅዱስ ጳውሎስ ለ) ቅዱስ ጴጥሮስ ሐ) ሁለቱም

፪- ጌታችን ስለ ምን ታሳድደኛለህ በማለት ከክፉ ሥራው ላይ ለአገልግሎት የመረጠው ሐዋርያ ማነው?

ሀ) ቅዱስ ጳውሎስ ለ) ቅዱስ ጴጥሮስ ሐ) ሁለቱም

፫- ጌታችን አስቀድሞ ከመረጣቸው ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መካከል እንደ አንዱ ሆኖ የሚቆጠረው የትኛው ሐዋርያ ነው?

ሀ) ቅዱስ ጳውሎስ ለ) ቅዱስ ጴጥሮስ ሐ) ሁለቱም

፬- ሕግን ጠንቅቆ የተማረና በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ያልኖረ፡-

ሀ) ቅዱስ ጳውሎስ ለ) ቅዱስ ጴጥሮስ

ሐ) ሁለቱም

፭- መጽሐፍን የማያውቅና ያልተማረ ተብሎ የተነገረለት ሐዋርያ ማነው?

ሀ) ቅዱስ ጳውሎስ ለ) ቅዱስ ጴጥሮስ ሐ) ሁለቱም

፮- ለተገረዙት የሆነው የወንጌል አደራ የተሰጠው ለየትኛው ሐዋርያ ነው?

ሀ) ቅዱስ ጳውሎስ ለ) ቅዱስ ጴጥሮስ ሐ) ሁለቱም

፯- ላልተገረዙት ወይም ለአሕዛብ የወንጌል አደራ የተሰጠው፡-

ሀ) ቅዱስ ጳውሎስ ለ) ቅዱስ ጴጥሮስ ሐ) ሁለቱም

፰- በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም። የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል። ተብሎ በጌታ የተነገረለት፡-

ሀ) ቅዱስ ጳውሎስ ለ) ቅዱስ ጴጥሮስ ሐ) ሁለቱም

፱- የእኔን እግር ለዘላለም አታጥብም በማለት ለጌታ የመለሰና በኋላም እግሬን ብቻ ሳይሆን እጄንና እራሴንም እጠበኝ ያለው ሐዋርያ ማነው?

ሀ) ቅዱስ ጳውሎስ ለ) ቅዱስ ጴጥሮስ ሐ) ሁለቱም

፲- መንፈስ ቅዱስን የመስጠት ኃይልና ድንቅና ተአምራት በማድረግ የታወቀው ሐዋርያ ማን ይባላል?

ሀ) ቅዱስ ጳውሎስ ለ) ቅዱስ ጴጥሮስ ሐ) ሁለቱም

፲፩- ሙታንን ያሥነሣና ስሙም በጌታ የተቀየረለት ሐዋርያ ማነው?

ሀ) ቅዱስ ጳውሎስ ለ) ቅዱስ ጴጥሮስ

ሐ) ሁለቱም

፲፪- በደለኞችን በመቅጣትና የወንጌልን ቃል ለማስተማር ብርቱና ደፋር የነበረ ሐዋርያ ማነው?

ሀ) ቅዱስ ጳውሎስ ለ) ቅዱስ ጴጥሮስ ሐ) ሁለቱም

፲፫- እጅግ በጣም ትሁትና ለብዙ ስደትና ፈተና የተጋለጠ ሐዋርያ፡-

ሀ) ቅዱስ ጳውሎስ

ለ) ቅዱስ ጴጥሮስ

ሐ) ሁለቱም

፲፬- አይሁድ አንድ ሲጎድል አርባ ግርፋት አምስት ጊዜ ገረፉኝ። ሦስት ጊዜ በበትር ተመታሁ፤... ብዙ ጊዜ በመንገድ ሄድሁ፤ በወንዝ ፍርሃት፥ በወንበዴዎች ፍርሃት፥ በወገኔ በኩል ፍርሃት፥ ... ነበረብኝ፤ ... በራብና በጥም ብዙ ጊዜም በመጦም፥ በብርድና በራቁትነት ነበርሁ። የቀረውንም ነገር ሳልቆጥር፥ ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው። በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረበት መልእክት ምዕራፍና ቁጥር፡-

ሀ) ፩ቆሮ.፲፩፥፳፩-፳፰ ለ) ፩ቆሮ.፳፩፥፳፩-፳፰

ሐ) ፪ቆሮ.፳፰፥፳፩-፳፰ መ) ፪ቆሮ.፲፩፥፳፩-፳፰

፲፭- የሰማዕትነትን አክሊል የተቀዳጀና ክብረ በዓሉም በሐምሌ ፭ ቀን የሚከበርለት ሐዋርያ ማን ይባላል?

ሀ) ቅዱስ ጳውሎስ ለ) ቅዱስ ጴጥሮስ

ሐ) ሁለቱም

፲፮- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በቀደመ ስሙ ማን ተብሎ ይታወቃል? ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስስ?

________________________________________

፲፰- በአንድ ጊዜ ሦስት ሺህ ሰዎች በትምህርቱ አምነው የተጠመቁለት ሐዋርያ ማነው?

________________________________________

፲፱- ቁልቁል ተሰቅሎ ሕይወቱን ያጣው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲሆን አንገቱ በሰይፍ ተቀርጦ ሕይወቱን ያጣው ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ነው። እውነት/ ሐሰት

፳- የመውጊያውን ብረት ብትቃወም በአንተ ይብስብሃል በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን የተናገረው ማነው?________________________________

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

አብርሃም ሰሎሞን

# የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እና ጤና



የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ ጤናማ ክብደትን ከመጠበቅ ባሻገር የኮለስትሮልንና የደም ግፊትን መጠን ለመቀነስ ያስችላል። እድሜያቸው ከአሥራ ስምንት ዓመት በላይ ያሉ ጎልማሶች በሳምንት ውስጥ ባሉት አብዛኛው ቀናት ከግማሽ ሰዓት ያላነሰ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ እንደሚገባቸው የ ዩናይትድ ስቴትስ ዋና የጤና ጥበቃ ማእከል ያዛል።

መደበኛና ተከታታይ የሆነ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ ለጤናዎ መጠበቅ ከሚያደርጉዋቸው ነገሮች ሁሉ በዋነኛነት ሊከተታተሉት የሚገባ ነው።
የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ዋና ዋና ጥቅሞች:-

- ክብደትዎን ለመቆጣጠር
- በልብ በሽታ የመታመም እድልዎን ለመቀነስ
- የሁለተኛው ዓይነት የስኳር በሽታና ተዛማች የሆኑ የጤና እክሎችን ለመቀነስ በጥቅል ስሙ metabolic syndrome የሚባለውን ዘርፈ ብዙ የጤና ቀውስ እድል ለመቀነስ ይረዳናል፤ ይኼውም በሆድና ዳሌ ላይ የሚከማች ስብን፤ ከፍተኛ የደም ግፊትን ፤ከፍተኛ የደም ስኳር መጠንና በደም ውስጥ ያሉ ስብ ነክ ንጥረ ነገሮችን (triglycerides) ለመቀነስ) እና ጥሩ የሚባለውን ኮሎስተሮል ዓይነት ለመጨመር ይረዳናል።

- በአንዳንድ የካንሰር ዓይነቶች የመታመም እድልዎን ለመቀነስ
- አጥንትዎንና ጡንቻዎን ለማጠንከር
- የአእምሮ ጤናዎን ለማሻሻል
- ረጅም እድሜ ለመኖር ያልዎትን እድል ለመጨመር

የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎን ለመጨመርና ጤናዎን ለማሻሻል በቅድስት ሥላሴ የአምስት ሺህ ርምጃና ሩጫ ላይ ለመሳተፍ ይዘጋጁ። ትኬት በድረ ገጽ ላይ መግዛት ይችላሉ፡፡ www.minnesotaselassie.org/5k

በተጨማሪም ቅዳሜ ጠዋት በሚደረገው የእግር ኳስ ልምምድ ላይ እርስዎና ቤተሰብዎ ይሳተፉ።
አድራሻ፡ Pearl Park, Portland Ave. and E 53rd S — close to 5288 Portland Ave S, Minneapolis, MN


በአንድነት ተሰባስበው የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ላይ ለመሳተፍ ባይችሉ እንኳ ከማኅበረሰብዎ ጋር እርስ በራስ ለመበረታታትና ለመወዳደር ብሎም እንቅስቃሴዎን ለመጨመር የጤና ክፍላችን ባዘጋጀው ድረ ገጽ ላይ ተመዝግበው የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎን ይጨምሩ።
https://app.inkin.com/group/631/contest/list

ለተጨማሪ መረጃ የሚከተለውን ድረ ገጽ ይመልከቱ:-
Physical Activity and Health
https://www.cdc.gov/physicalactivity/basics/pa-health/index.htm

ይስሐቅ ቱራ (RN)
የምእመናን የጤና አገልግሎት ክፍል
Faith Community Health Program




**ነጻ የጤና ምርመራ 5ሺ ሩጫ በሚካሄድበት ቀን**




BlueCross BlueShield is sponsoring it's first Health Village, to be hosted at the Kidist Selassie 5K on July 29, at Phalen Park. Free health screenings and health education booths. Please stop by each booth. Health screening participants will receive incentives.

**ሥራህን ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ፥ አሳብህም ትጸናለች። ምሳ ፲፮፥፫**



የርእሰ አድባራት ጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ ተቋማት ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ቆይተው ከሁለተኛ ደረጃ እና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለተመረቁ ምዕመናን ቡራኬ ከደብሩ አስተዳዳሪ መልአከ አርያም ቆሞስ አባ ኃይለሚካኤል May 21, 2017 እንዲቀበሉ አደረገች። በዓይነቱ የመጀመሪያ በሆነው በዚህ ዝግጅት ላይ 26 ተመራቂዎች በዝርዝር የቀረቡ ሲሆን፤ ከሁለተኛ ደረጃ ጀምሮ እስከ ዶክትሬት ዲግሪ ድረስ ትምህርታቸውንን ያጠናቀቁ ምዕመናን ተገኝተውበታል። ተመራቂዎች ወደ አውደ ምሕረት እየተጠሩ ቡራኬ ሲቀበሉ የቤዛ ኲሉ ሰንበት ትምህርት ቤት ዘማርያን እና ምዕመናን "እግዚአብሔር ይመስገን ለዚህ ላደረሰን" የሚለውን መዝሙር በመዘመር ለእግዚአብሔር ምስጋናን አቅርበዋል።

ከቡራኬው በኋላ የደብሩ አስተዳዳሪ የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል። በመልዕክታቸውም ከሁለተኛ ደረጃ ለተመረቁት በሚቀጥለው የትምህርት ቤት ጉዟቸው ላይ በማተኮር እንዲበረቱ አሳስበው በተጓዳኝ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሳይርቁ እንዲጓዙ መክረዋል። ወላጆችም በዚህ ጉዳይ ክትትል በማድረግ እንዲያበረቷቸው በአንክሮ አሳስበዋል። ከዛም በመቀጠል በመጀመሪያ እና በከፍተኛ ትምህርት ዲግሪያቸውን የተቀበሉትን ተመራቂዎች በተለያዩ የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ክፍሎች ውስጥ በመሳተፍ በየሙያቸው እንዲያገለግሉ በመምከር እግዚአብሔርም በሚሠሩት ሁሉ እንዲረዳቸው አባታዊ ቡራኬ ሰጥተዋል።

ከቅዳሴ በኋላም በደጀ ሰላም ውስጥ በተደረገው ዝግጅት ተመራቂዎች ራሳቸውን በማስተዋወቅ ምን እንደተማሩና ወደፊት ምን ሊማሩ እንዳቀዱ ለተሰበሰበው እድምተኛ ገልጸዋል። በተለይም በመቶዎች የሚቆጠሩ ሕፃናት ከተመራቂዎች ፊት ለፊት ተቀምጠው ይኽንን ደስታ አብረው እንዲካፈሉ መደረጉ ምዕመናንን ካስደሰቱ ጉዳዮች ዋነኛ እንደሆነና ሕፃናቱም ላይ የሚፈጥረው ገንቢ ተጽእኖ በማሰብ ይኽን ዓይነቱ ዝግጅት ሊበረታታ እንደሚገባው ብዙዎች ሐሳብ ለግሰዋል።

በወቅቱ በእንግድነት በቤተ ክርስቲያናችን የተገኙት መጋቢ ጥበብ በእምነት በቀለ ከእራሳቸው የትምህርት ጉዞ ተመክሮ በመነሳት ተመራቂዎችን የበለጠ በትምህርታቸው እንዲገፉ የሚያነሳሳና በተማሩበት ሙያ ሃገራቸውን እና ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲያገለግሉ የማይረሳ ምክር አስተላልፈዋል። በተጨማሪም መጋቢ ጥበብ ፊት ለፊት ተቀምጠው በጥሞና የሚከታተሉትን ሕፃናት እየተደረገ ስላለው ሂደት ሊረዱት በሚችሉበት ቋንቋ አብራርተው፤ ሕፃናቱም በርትተው በመማር በዕለቱ ተመራቂዎች የያዙትን ቦታ እነሱም እንደሚይዙት በእርግጠኝነት ገልጸዋል።

ቀጥለውም ሕፃናቱ ያላቸውን ማንኛውንም ጥያቄ ለተመራቂዎች እንዲጠይቁ እድል ከፍተዋል። በመጀመሪያ እድል የተሰጠው የ6 ዓመት ሕፃን ልጅ "ከተመራቂዎች ፊት የተደረደረውን ኬክ፤ ተመራቂዎች ብቻ ናቸው ወይ የሚበሉት?" ብሎ በመጠየቅ በደጀ ሰላም የተሰበሰበውን ምዕመን በጣም አስቋል። ተመራቂዎች ከሕፃናቱ የቀረቡላቸውን ጥያቄዎች ካስተናገዱ በኋላ በመጋቤ ኀሩያን ቀሲስ መጽናኛዬ ምክር እና የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት የዕለቱ መርሐ-ግብር በደስታ እና በምስጋና መንፈስ ተቋጭቷል። ይህን ላደረገ አምላካችን ክብርና ምስጋና ይግባው። ተመራቂዎች እና ወላጆች እንኳን ደስ አላችሁ። ይኽንን ፕሮግራም እንዲሳካ ላደረጋችሁ ምዕመናን ሁሉ እግዚአብሔር ይስጣችሁ።

## High School

1. BedeMariam Tsegaye
2. Dina Teferi
3. Egeziharya Yilma
4. Kidist Chaka
5. Ledet Bayou
6. Meron Negash
7. Michael Mamo
8. Teferi Belete
9. Tensae Mekonnen
10. Yacob Yisehak
11. Zablon Teferi
12. Hana Dereje

## College/University

1. Abenet Wordofa (St. Paul College: CNC Machine Tool Making)
2. Bethlehem Alem (St. Cloud State University: Biomedical Science)
3. Daniel Cheriye (University of Minnesota: MD)
4. Daniel Yilma (St. Thomas: MS in Elect. Engineering)
5. Frezer Yimer (Hamline: MBA)
6. Hewan Redie (Metro State University: Comp. Science)
7. Lelna Desta (St. Thomas: MBA)
8. Lilli Terefe (St. Paul College: Licensed Practical Nursing)
9. Mariam Tadesse (Hamline: Political Sci.; Minor Law)
10. Million Woldehawariat (Hamline: MBA)
11. Nuela Elias (St. Cloud State University: International Business Marketing; Minor Economics)
12. Ruth Mamo (University of Minnesota: Biology)
13. Saron Kassahun Chekol (St. Cloud State University: Biomedical Sciences and minor in Chemistry)
14. Tsigereda Abebe (University of Minnesota: Biology)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

ዶ/ር ኤልያስ አያና

ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር ላይ ከቦታ ቦታ እየተመላለሰ ካከናወናቸው ድርጊቶች አንዱ ደቀ መዛሙርትን እንዲሁም ሌሎችን አርድእት (ረዳቶችን) በመምረጥ ሥራ እንዲሠሩ ማድረግ ነበር። በምክርም ሲያጸናቸው የሚልካቸው እንደ በጎች በተኵላዎች መካከል እንደሆነና ሥራቸውም ቀላል እንዳልሆነ አስተምሯቸዋል። ወደ ከተሞች በመሄድ በዚያ ድውይ እንዲፈውሱና የእግዚአብሔርን ቃል እያስተማሩ ወደ መንግሥቱ እንዲያቀርቡ ሥልጣን ሰጣቸው። በተለይም አጋንንት በእርሱ ስም ከሰዎች እንዲወጡ ማድረጋቸው ያስደሰታቸው አርድእት፥ “ጌታ ሆይ፥ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል” ባሉት ጊዜ ጌታችን ሲመልስ “… በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጎዳችሁም ምንም የለም። ነገር ግን መናፍስት ስለተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ፥ ስማችሁ ግን በሰማያት ስለተጻፈ ደስ ይበላችሁ።” ብሏቸዋል። (ሉቃ ፩፥ ፱-፳)

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን እንደ ክርስቶስ አካልነቷ እርሱን ወክላ እንደ እርሱ ሆና እንድትኖርና እንድትሠራ ጌታ ፈቅዶላታል። ቤተ ክርስቲያንንም እንዲጠብቋት የሾማቸውን ሐዋርያት የእርሱ እንደራሴዎች አድርጓቸዋል። ይህንም ሲያሳይ ጌታችን በመጀመሪያ ለሐዋርያት፣ ቀጥሎም ለተተኪዎቻቸው "የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል፥ እናንተንም የጣለ እኔን ይጥላል፤ እኔንም የጣለ የላከኝን ይጥላል።" ብሏቸዋል። (ሉቃ ፲፥፲፮) የቤተ ክርስቲያናችን አባቶች ካህናት፥ ምእመናኑን ለመጠበቅና ለማስተዳደር ከፍተኛ ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል። በተለይም መንጋውን በመጠበቅ ለነፍሳት አባትና እረኛ ለሆኑት ሁሉ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊነት እንደሚጠብቃቸው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ያስጠነቅቃል። (የሐዋ ፳፥፳፰-፴)

በቤተ ክርስቲያን ለሚካሄዱት መንፈሳዊና ማኅበራዊ ተግባራት መሳካት ካህናት ብቻ ሳይሆኑ ምእመናንም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ይህም ክፉውን በማስወገድ የቅድስናን ኑሮ በመኖርና መልካም አርአያነትን በማሳየት፥ የፍቅርና የጽድቅን ሥራ በመሥራት፥ ችግረኞችን በመርዳት፥ ምጽዋትና ልዩ ልዩ አስተዋጽኦ በማድረግ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጎልቶ የሚታይ ኃላፊነት አለባቸው።




ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የሁላችንም ናት። በጠቅላላ ጉባኤው የተመረጡት አሥራ አንዱ የሰበካ ጉባኤ አባላት የሚያወጡትን የሥራ ዕቅድ መተግበር የሚችሉት የሁላችንም ድጋፍ ሲጨመርበት ብቻ ነው። እግዚአብሔር አምላካችንም ይህን መተባበራችንንና አንድነታችንን ሲመለከት በበለጠ በረከት ያትረፈርፈናል። በተለያዩ ንዑሳን ኮሚቴዎች ውስጥ እያገለገልን የምንገኝ አባላት ስማችን በሰማያት ስለተጻፈ እጅግ በጣም ደስ ሊለን ይገባል። ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ወደፊትም ቢሆን የጀመረችውን ይህን መጠነ ሰፊ አገልግሎት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መቀጠል ያስችላት ዘንድ ከሁላችንም ያላሰለሰ መንፈሳዊ ትጋት ያስፈልጋል። ጌታችን ለአርድእቱ እንዳስተማረው ምድራዊ ምሥጋናን በመናቅ ሰማያዊውን ሀብት በመሻት እስከ መጨረሻው ተሳትፎአችንን መቀጠል ይኖርብናል። በተለይም ደግሞ በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ላለብን የሀገረ ስብከት ስብሰባ አስተናጋጅ አጥቢያ እንደመሆናችን ከካህናቱ አንሥቶ ማንኛውም ምእመን በኅብረት መሳተፍ ይኖርብናል፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን በመገንባት ለሀገረ ስብከት ስብሰባ መመረጣችንን በማሰብ አገልግሎታችንን እናጠናክር።

እግዚአብሔር አምላክ የጀመርነውን አዲስ ምዕራፍ እስከመጨረሻው ጠብቆልን የመንግሥቱ ወራሾች እንሆን ዘንድ የእርሱ ቅዱስ ፈቃድ፣ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት፣ የቅዱሳን በረከት አይለየን፥ አሜን።

ወይትባረክ አምላከ አበዊነ

የርእሰ ደብሩ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ

2017 Kidist Selassie 5k Sponsors

PREMIERE SPONSOR
BlueCross BlueShield Minnesota

PLATINUM SPONSOR
Dream Homes Inc.
TRANSFORMING ASPIRATIONS INTO REALITY

GOLD SPONSOR
Kidist Selassie Faith Community Health Program

SILVER SPONSORS
FAIRVIEW | HD Laundry | Dilla Restaurant
Universal Realty Demissie Kebede
Ashama Grocery & Meat Market
Shebelle Grocery & Restaurant
Samson Custom Upholstery
Esegenet Lema Edina Realty
Shega Injera | Bremer Bank
Sharp 360 Men's Clothing
Tropicana Cafe St Paul
Carepoint Dental